በኢትዮጵያ የሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት የሚቲዎሮሎጂ ትንበያ፣ ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ እና ምክር አገልግሎት ምርምር ዘርፍ



# የአስር ቀን የአየር ሁኔታ ግምገማ እና ትንበያ መጽሔት

## ከፌብርዋሪ 21-29/2024 የነበረው የአየር ሁኔታ ግምገማ እንዲሁም

## ከማርች 1-10፤11-20/2024

## የሚኖረው የአየር ሁኔታ ትንበያ እና ምክረ ሃሳብ

ማርች 2024

አዲስ አበባ

ስልክ +251115538394 ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡nma1@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

**ርዕስ** **ገፅ**

**እ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 21 እስከ 29/2024 የነበረው የአየር ሁኔታ ግምገማ** ........ - 1 -

ካርታ 1 እ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 21 እስከ 29/2024 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ ........ - 2 -

ካርታ 2 እ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 21 እስከ 29/2024 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸዉ ቀናት ........ - 2 -

ካርታ 3 እ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 21 እስከ 29/2024 ድረስ የነበረዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር ........ - 2 -

ምስል 1 የቀኑ ከፍተኛ የሙቀት መጠን በዲ.ሴ ........ - 3 -

እ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 21 እስከ 29 /2024 የነበረው የአየር ሁኔታ በግብርና ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ ........ - 3 -

ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከፌብሩዋሪ 21 እስከ 29/2024 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ ........ - 4 -

እ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 21 እስከ 29/2024 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ- 4 -

ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከፌብሩዋሪ 21 እስከ 29/2024 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ ........ - 4 -

እ.ኤ.አ ከማርች 1 እስከ 10/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ ........ - 5 -

ካርታ 6 እ.ኤ.አ. ከማርች 1-10, 2024 የሚኖረዉ የቀኑ ከፍተኛ የሙቀት መጠን በዲ.ሴ ........ - 6 -

ካርታ 7 እ.ኤ.አ. ከማርች 1-10, 2024 የሚኖረዉ የዝናብ መጠን በሚ.ሜ ........ - 6 -

እ.ኤ.አ ከማርች 11 እስከ 20/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ ........ - 6 -

እ.ኤ.አ ከማርች 1 እስከ 10/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በእርሻ ሥራ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ ........ - 7 -

እ.ኤ.አ ከማርች 1 እስከ 10/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በዉሀዉ ዘርፍ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ ........ - 7 -



ስልክ +251 115538394 ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡ nma1@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

# እ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 21 እስከ 29/2024 የነበረው የአየር ሁኔታ ግምገማ


ባለፉት ቀናት በደቡብ፣ በደቡብ ምዕራብ፣ በመካከለኛው፣ በሰሜን ምስራቅ እና በምስራቅ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ ጠንካራ የደመና ሽፋን እና ክምችት ነበራቸው፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞ በመካከለኛው፣ በሰሜን ምስራቅ፣ በደቡብ እና በደቡብ ምዕራብ የአገሪቱ ክፍሎች ላይ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለዉ ዝናብ ተመዝግቧል፡፡ ከቀላል እስከ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ከተመዘገበባቸው የሚቲዎሮሎጂ ጣቢያዎች መካከል በአዲስ አበባ ቦሌ 8.6፣ 56.2 በአዲስ አበባ 5.6፣ 2፣ በሃዋሳ 6፣ በቢሾፍቱ 8፣10.6፣ በጎሬ 6.፣ በጅማ 2.6፣ ሮቤ 30.4፣ 12.6፣ በአይራ 5.5፤ አለም ተፈሪ 2.6፣ በአማን 6.1፣11.2፣ 26.8 እና 11.2፣ አንገር ጉትን 8.6፣ በበደሌ 3.4፣ በብላቴ 2.5፣ 24.2፣ በጨፋ 5.6፣ 5.6 በደብረ ብርሃን 3.6፣ በደምቢ ዶሎ 5.2፣ በፍቼ 5.3፣ በጋቲራ 20.4፣ 29.6፣ በሆሳና 8.8፣ በቁለምሳ 26.8 ፣ በጂንካ 22.9፣ 25.4፣ 5.1 በማጂ 11፣ በሳውላ 5.2፣ 10.2፣ 30.8፣ በአቦምሳ 36.6 በሻምቡ 9.5፣ በቴፒ 10.3፣ 4.9፣ በተርጫ 12.5፣ በወላይታ ሶዶ 2.3፣ እንዲሁም በባቱ 5.6 በሚ.ሜ ይገኙበታል።

ባለፉት ቀናት የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከሀገሪቱ ቦታ ሽፋን አንፃር ሲገመገም፤ ሁሉም የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ዞኖች፣ የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ዞኖች፣የሲዳማ ክልል ዞኖች፣ ከማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ስልጤ እና ጉራጌ ዞኖች፤ ከኦሮሚያ ኢሉባቦር፣ ቡኖ በደሌ፣ጂማ፣ ሁሉም የሸዋ ዞኖች፣ አርሲ አና ምዕራብ አርሲ፣ ምዕራብ ጉጂ፣ቦረና ዞኖች፤ አዲሰ አበባ ላይ ከ6-51 ሚ.ሜ የሚደርስ ዝናብ ከ2-4 ቀናት ያህል ዝናብ ነበራቸዉ (ካርታ 1 እና 2) ፡፡


ባለፉት ዘጠኝ ቀናት የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር ሲነፃፀር ከጋምቤላ ክልል የማዣንግ ዞን፤ ከአማራ ክልል የሰሜን ሸዋ ዞን፣ ከኦሮሚያ ክልል ምስራቅ ወለጋ፣ ምስራቅ ሸዋ፣ አርሲ፣ ምሰራቅ ጉጂ እና ቦረና፤ ከሱማሌ ክልል የዳዋ ዞን፤የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ዞኖች፤ ከደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ደቡብ ኦሞ፣ ኮንሶ፣ ጎፋ፣ጋሞ እና የጌዲዮ ዞኖች መደበኛና ከመደበኛ በላይ የሆነ የዝናብ መጠን አግኝተዋል (ካርታ 3) ፡፡




ስልክ +251115538394 ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡nma1@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et




ካርታ 1 እ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 21 እስከ 29/2024 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ




ካርታ 2 እ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 21 እስከ 29/2024 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸዉ ቀናት





ካርታ 3 እ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 21 እስከ 29/2024 ድረስ የነበረዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር



ስልክ +251 115538394 ፋክስ 0115517066 ኢ.ሜይል፡ nma1@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

በሌላ በኩል በሰሜን ምዕራብ፤ ጋምቤላና በደቡብ ምስራቅ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ የቀኑ ከፍተኛ የሙቀት መጠን ከ35.2-42.6 ዲግሪ ሴልሽየስ ተመዝግቧል (ምስል 1) ።





ምስል 1 የቀኑ ከፍተኛ የሙቀት መጠን በዲ.ሴ

## እ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 21 እስከ 29 /2024 የነበረው የአየር ሁኔታ በግብርና ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባለፉት ቀናት በአብዛኛዎቹ የበልግ አብቃይ በሆኑት የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው የእርጥበት ሁኔታ ነበራቸው፡፡ ይህም ሁኔታ የአፈር ውስጥ እርጥበትን በማሻሻል የበልግ ወቅት ሰብሎችን በወቅቱ ለመዝራት፤ ለቋሚ ተክሎች የውሃ ፍላጎት መሟላት እንዲሁም ለአርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች የግጦሽ ሳርና የመጠጥ ውሃ ፍላጎትን ከማሟላት አንጻር ከፍተኛ ጠቀሜታ ነበረው (ካርታ 4)፡፡




ስልክ +251 115538394 ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡ nma1@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et




ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከፌብሩዋሪ 21 እስከ 29/2024 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ

## እ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 21 እስከ 29/2024 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባለፉት ቀናት በባሮአኮቦ፣ በመካከለኛው እና በታችኛው ኦሞጊቤ፣ በታችኛው ስምጥ ሸለቆ እና በገናሌ ዳዋ አዋሳኝ ተፋሰሶች ላይ ከእርጥበታማ እስከ ከፍተኛ የእርጥበት ሁኔታ ነበራቸው፡፡ በተጨማሪም በጥቂት የላይኛው እና መካከለኛው ገናሌዳዋና ስምጥ ሸለቆ እንዲሁም በዋቤ ሸበሌ አዋሳኝ ተፋሰሶች መጠነኛ የእርጥበት ሁኔታ ስር ቆይተዋል (ካርታ 5) ፡፡




ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከፌብሩዋሪ 21 እስከ 29/2024 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ



ስልክ +251 115538394 ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡ nma1@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

## እ.ኤ.አ ከማርች 1 እስከ 10/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ

በመደበኛ ሁኔታ በማርች የመጀመሪያው አሥር ቀናት ለበልግ ዝናብ መፈጠር አመቺ የሆኑ የአየር ሁኔታ ክስተቶች ከዕለት ወደ ዕለት እየተጠናከሩ የሚሄዱበት ወቅት ነው፡፡ በመሆኑም በበልግ አብቃይ አከባቢዎች የዝናቡ መጠንና ስርጭት እየተስፋፋና እየተጠናከረ ይመጣል፡፡


በሚቀጥሉት አሥር ቀናት ለዝናብ መፈጠር አስተዋጽኦ የሚያደርጉ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች እንደሚጠናከሩ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማለ፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘም በደቡብ፤ በሰሜን ምስራቅ፣ በምስራቅ፣ በመካከለኛዉ፣ በደቡብ ምዕራብ እንዲሁም በስምጥ ሸለቆና አጎራባች አካባቢዎች የተሻለ ጥንካሬ ይኖራቸዋል (ካርታ 7)፡፡ በመሆኑም በበልግ አብቃይ አከባቢዎች በርካታ ቦታዎቻቸውን የሚሸፍን ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ ያገኛሉ (ካርታ 7)፡፡ በተጨማሪም አልፎ አልፎ ከሚጠናከሩት የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ላይ በመነሳት በደቡብ፤ በመካከለኛዉ፣ በሰሜን ምስራቅ እና በደቡብ ምዕራብ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚያገኙ አሃዛዊ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ (ካርታ 7 )፡፡

በአጠቃላይ በሚቀጥሉት ቀናት ከኦሮሚያ ክልል ጅማ፣ ሁሉም የሸዋ ዞኖች፣ ምዕራብ አርሲና አርሲ ዞኖች፣ ባሌ፣ ምዕራብ ጉጂ፤ አዲስ አበባ፤ ከአማራ ክልል ምስራቅ ጎጃም፣ የሰሜንና የደቡብ ወሎ ዞኖች፣ የዋግህምራ ዞኖች፣ እንዲሁም የሰሜን ሸዋና የኦሮሚያ ልዩ ዞን፤ የሲዳማ ክልል ዞኖች፤ የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ዞኖች፤ የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ዞኖች፤ የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ዞኖች፤ ከመደበኛ ጋር የተቀራረበ ዝናብ የሚኖራቸው ሲሆን፤ በጥቂት ስፍራዎቻቸው ላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ያገኛሉ (ካርታ 7)፡፡ በተጨማሪም ቡኖ በደሌ፣ ኢሉባቦር፣ ጉጂ፣ የቦረና ዞን፣ ምዕራብና ምስራቅ ሐረርጌ፣ ምስራቅ ባሌ፤ እንዲሁም ሐረሪ እና ድሬዳዋ፤ የደቡብ ጎንደር ዞኖች፤ የአፋር ክልል ዞኖች፤ ከትግራይ ክልል የደቡብ፣ የደቡብ ምስራቅ እና የምስራቅ ትግራይ ክልል ዞኖች፤ ከሱማሌ ክልል የሲቲ፣ የፋፈን፣ የዳዋ እና ጥቂት የሊበን ዞኖች ቀላል መጠን ያለው




ስልክ +251 115538394 ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡ nma1@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

ዝናብ ያገኛሉ (ካርታ 7)። በሌላ በኩል በጋምቤላ፤ በሰሜን ምዕራብ፤ በሰሜን ምስራቅና በደቡብ ምስራቅ አከባቢዎች ላይ የቀኑ ከፍተኛ የሙቀት መጠን ከ 38 ዲግሪ ሴልሺየስ በላይ እንደሚሆን የትንበያ መረጃዎች ያሳያሉ (ካርታ 6)።




ካርታ 6 እ.ኤ.አ. ከማርች 1-10, 2024 የሚኖረዉ የቀኑ ከፍተኛ የሙቀት መጠን




ካርታ 7 እ.ኤ.አ. ከማርች 1-10, 2024 የሚኖረዉ የዝናብ መጠን በሚ.ሜ

## እ.ኤ.አ ከማርች 11 እስከ 20/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ

በመደበኛ ሁኔታ ከማርች አጋማሽ በኋላ የወቅቱ ዝናብ አብዛኛውን የበልግ ዝናብ ተጠቃሚ አካባቢዎችን የሚሸፍን ሲሆን፤ ከዚሁ ጋር ተያይዞም የሰሜን ምሥራቅ፣ የምሥራቅ፣ የደቡብና የደቡብ ምሥራቅ የሀገሪቱ አከባቢዎች በመጠንም ሆነ በሥርጭት የተስፋፋና የተጠናከረ ዝናብ ያገኛሉ፡፡

በሚቀጥሉት አሥር ቀናት አሁን እየተስተዋለ ያለዉ ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች በአብዛኛዎቹ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ ይበልጥ እየተጠናከሩ እንደሚሄዱ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ ከዚሁም ጋር ተያይዞ ከሚጠናከሩት የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ላይ በመነሳት አልፎ አልፎ በሚኖሩት ቀናት በተለይም በደቡብ ምዕራብ፣ በመካከለኛ፣ በሰሜን ምስራቅ እና በምስራቅ የሀገራችን አከባቢዎች ላይ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚኖራቸዉ አሃዛዊ የትንበያ መረጃዎች ያመላክታሉ ፡፡



ስልክ +251 115538394 ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡ nma1@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

## እ.ኤ.አ ከማርች 1 እስከ 10/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በእርሻ ሥራ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥሉት የማርች የመጀመሪያው አስር ቀናት በበልግ አብቃይና እርጥበት ተጠቃሚ በሆኑ የሀገሪቱ ክፍሎች ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው የእርጥበት ሁኔታ የሚያገኙ ሲሆን፤ አልፎ አልፎ በጥቂት ቦታዎቻቸው ላይ ከፍተኛ የሆነ የእርጥበት መጠን እንደሚያገኙ ይጠበቃል። ይህም ሁኔታ የአፈር ውስጥ እርጥበትን በማሻሻል የበልግ ወቅት ሰብሎችን በወቅቱ ለመዝራት፣ ለቋሚ ተክሎች የውሃ ፍላጎት መሟላት እንዲሁም ለአርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች የግጦሽ ሳርና የመጠጥ ውሃ አቅርቦትን ከማሟላት አንጻር አዎንታዊ ሚና ይኖረዋል፡፡ ከዚህም ጋር ተያይዞ አርሶ አደሮች እና የሚመለከታቸው የዘርፉ አካላት አስፈላጊውን ግብዓት ከወዲሁ በማዘጋጀት የበልግ አብቃይ በሆኑት አካባቢዎች አስፈላጊው ቅድመ ዝግጅት እና ትግበራ ስራዎችን ማከናወን ያስፈልጋል፡፡

## እ.ኤ.አ ከማርች 1 እስከ 10/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በዉሀዉ ዘርፍ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥሉት አስር ቀናት በላይኛው እና በመካከለኛው ኦሞ ጊቤ፣ በስምጥ ሸለቆ፣ በአዋሽ፣ በመከከለኛው ምስራቃዊ አባይ፣ በላይኛው ባሮ አከቦ፣ በአፋር ደናክል፣ በጥቂት የላይኛው ገናሌ ዳዋ እና በተከዜ ተፋሰሶች ላይ ከመጠነኛ እርጥበት እሰከ እርጥበታማ የአየር ሁኔታ ይኖራቸዋል፡፡



ስልክ +251 115538394 ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡ nma1@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et